የሰ/መ/ቁ 39529

ግንቦት 11 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሀጎስ ወልዱ

ሂሩት መሰሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ቦሌ ክ/ከተማ የመሬትና ልማት አስተዳደር ነ/ፈ ደረጀ ቀረበ

**ተጠሪ፡-** 1. ወ/ሮ ግምጃ በዳኔ - በራሳቸውና ሞግዚት በሆኑላት በህፃን ብሩክ ባጫ ስም

ወኪል ብርቱካን ባጫ ቀረቡ

2. ወ/ሮ ሮማን ባጫ

3. ወ/ሮ ብርቱካን ባጫ

4. አቶ አሸናፊ ባጫ

5. ወ/ሪት መቅደስ ባጫ

6. ወ/ሮ ፋንቱ ባጫ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የሥር አንደኛ ተከሣሽ ተጠሪ ከሣሽ ነበሩ ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ አንደኛ አመልካች በተጠሪዎች እና በስር ሁለተኛ ተከሣሽ ሥም ካርታ ሰርቷል ተጠሪዎች ካርታውን ለመውሰድ ሲፈርሙ የሥር ሁለተኛ ተከሣሽ ለመፈረም ፍቃደኛ አልሆኑም፡፡ በመሆኑም አመልካች ተሰርቶ የተቀመጠውን ካርታ ይስጠን፣ የሥር ሁለተኛ ተከሣሽ ቀርበው እንዲፈርሙ ይወሰንልን ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

አንደኛ አመልካች በቀጠሮ ቀን መልሳቸውን ባለማያያዛቸው መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፎ የሥር ሁለተኛ ተከሣሽ መልስ ሲሰጡ (በፍሬ ጉዳዩ) በግሌ የሰራሁት የቤት ቁጥር 2026ን በቤት ቁጥር 443 ጋር ካርታው ስለተሰራ ለመፈረም አልገደድም፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር አግባብ ካለው ሕግና ከቀረበለት ማስረጃ አንፃር መርምሮ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በውሣኔውም የሥር ሁለተኛ ተከሣሽ ቀርበው የመፈረም ግዴታ እንዳለባቸው ተጠሪዎች በማስረጃ አላቀረቡም ስለዚህ ጥያቄውን ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም፡፡

አመልካች በሕግ ካርታ የመስጠት ሥልጣንና ግዴታ አለበት በዚህም የተነሣ ካርታ የሚጠይቀውን ወገን መብት አረጋግጦ ሲቀርብ አጣርቶ ካርታ የመስጠትም ሆነ የመከልከል ግዴታ የአመልካች ነው ተጠሪዎች የሟች ሚስትና ወራሽ መሆናቸውን በሟች ንብረት ላይ መብት እንዳላቸው አረጋግጠው ካርታ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡ በመሆኑም አመልካች የተጠሪን ጥያቄ በመቀበል ተጠሪዎች መብት ያላቸው መሆኑን አጣርቶ ካርታ ሊሰጣቸው ወይም የማይፈቀድበትን ምክንያት በመግለፅ ውሣኔ ሊሰጥ ይገባል ስለዚህ አመልካች የተጠሪዎችን ጥያቄ ተቀብሎ ክስ በቀረበበት ቤት ላይ መብት ካላቸው ካርታ እንዲሰጣቸው ሲል ወሰነ፡፡

አመልካችም በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ወደ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው በዚሁ ውሣኔ ባለመስማማት ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 18/2000 ባቀረበው አቤቱታ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ እና በፌዴራሉ ከ/ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል ሲል ጠይቋል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቷል፡፡ ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ላይ መብት ካላቸው አመልካች ካርታ ይሠጣቸው ተብሎ የመወሰኑ አግባብነት በመመርመር ነው፡፡

በዚህም መሠረት ይህን ነጥብ የግራ ቀኙ ወገን ካሰሙት ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ ባጭሩ ስናይ ተጠሪዎች በተሠጣቸውና በሥር ሁለተኛ ተከሣሽ ስም በአመልካች ካርታ ተሰርቶላቸው እያለ ተጠሪዎች ካርታውን ፈርመው ለመውሰድ ፍቃደኛ ሲሆኑ የሥር ሁለተኛ ተከሣሽ ካርታው የእኔ የግሌ የሆነውን ቤት አካቶ የተሰራ ስለሆነ ልፈርም አልገደድም ሲሉ ፍቃደኛ ያለመሆናቸውን በመግለፃቸው ምክንያት በቀረበው ክስ የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን ካየ በኂላ ተጠሪዎች መብት ካላቸው አመልካች ካርታ ይስጣቸው በማለት ወስኗል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤትም ጉድለት የለውም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

በእኛም በኩል ከሥር ፍ/ቤት የውሣኔ ሐተታ ልንገነዘብ እንደቻልነው አመልካች መብታቸውን አረጋግጦ የቀረቡለትን ወገኖች በእኩል የማስተናገድና አግባብ ያለው ምላሽ ሊሰጥ እንደሚገባው ገልጿል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ አመልካች በሕግ የተቋቋመ አስተዳደራዊ ተቋም በመሆኑ በሕግ በተሰጠው ሥልጣንና ሐላፊነት መሠረት አገልግሎት የሚሠጥ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡

እንግዲስ ከዚህ የአመልካች ሥልጣንና ተግባር ስንነሳ ሁለት መብት አለን ብለው የሚቀርቡለትን ወገኖች ሊያስተናግድ የሚችለው ባለው ሕጋዊ አሠራር ብቻ መሆኑን እንረዳለን በዚህ በተያዘው ጉዳይም ተጠሪዎች መብት አለን በማለት ካርታው እንዲሠጣቸው ጠይቀዋል፡፡ በተነጻጻሪ የሥር ሁለተኛ ተከሣሽም በጉዳዩ መብት አላቸው፡፡ ይሁን እንጂ የተሰራው ካርታ መጠን የግሌን ቤት አካቷል በማለት ቀርበው ሊቀበሉ (ሊፈርሙ) ፍቃደኛ አልሆኑም በመሆኑም በአመልካች በኩል እነዚህን ወገኖች አለን በሚሉት መብት ለማስተናገድ ይህ የጋራቸው የሆነውን ንብረት መቀበል የሚችሉት ፈቅደው በአመልካች መ/ቤት ቀርበው ፈርመው ሲቀበሉ ብቻ ነው፡፡ አመልካች እነዚህን ወገኖች አስተዳደራዊ ተግባሩን ከመወጣት ባሻገር ሊያስገድዳቸው የሚያስችለው አሰራር የሌለው መሆኑን መረዳት አያዳግትም፡፡ አመልካችም በክርክሩ እንደገለፀው በውሣኔ ተለይቶ ያልቀረበለትንና ሁለት ወገኖች መብት አለን ብለው ያቀረቡለትን ጉዳይ ሌላኛው ባለመብት ባልቀረበበትና ባልተስማማበት ለተጠሪዎች ብቻ አስፈርሞ መስጠቱ ሌላ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ተግባር ሊሆን ይችላል፡፡

በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት የሥር ሁለተኛ ተከሣሽን መብት ሣያገናዝቡ ተጠሪዎች መብት ካላቸው ካርታ ይሠጣቸው በማለት አመልካችን ማስገደዱ እና የፌ.ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህን ሣያርመው ማለፉ የአመልካችን አስተዳደራዊ ሥራ ላይ ጫና መፍጠር ነው፡፡

ባጠቃላይ ፍ/ቤቱም በጉዳዩ ስልጣን የለኝም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 231 መሠረት መዝገቡን መዝጋት ነበረበት፡፡

በመሆኑም የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 99300 በቀን 27/5/2000 እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 65637 ቀን 24/08/2000 የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ፍ/ቤቶች አመልካችን ካርታ እንዲሠጥ ሊያስገድዱ የሚችሉበት ሥልጣን የላቸውም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የግራ ቀኙ ይቻቻሉ

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ